# አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል

## ከአዲስ አበባ ከተማ ዳርቻ ላይ

## <u>ትዕይንት አንድ</u>

## 1. ድል በር አካባቢ

1.1 / ከአዲስ አበባ መውጫው ከዳገቱ ላይ ( ከመውጫው) በመሆን - ቁልቁል ከድል በር አካባቢ ካለው የመኪና መንገድ ላይ ያለው የመኪኖች እና የሰዎች እንቅስቃሴ እየታየ- አንዲት አነስተኛ አውቶቡስ ታክሲ (ሚኒ ባስ ታክሲ) - እየበረረች እና ... ከፊት ለፊቷ ያሉትን መኪኖች እየቀደመች...ወደ ሱሉልታ የሚወስደውን መንገድ ይዛ ስትመጣ ከርቀት እየቀረበች ትታያለች/

1.1.1 / ሁለት ወጣቶች በጠጡት መጠጥ የሞቅታ ስሜት ይነበብባቸዋል... ከመንገዱ በስተግራ ጥግ በኩል ካለው ቱቦ ውስጥ -ጎን ለጎን ቆመው ሽንታቸውን በመሽናት ላይ እያሉ ወደ እነሱ እየበረረች በመምጣት ላይ እያሉ ወደ እነሱ እየበረረች በመምጣት ላይ ያለችውን አነስተኛ አውቶቡስ ታክሲ ... ሲመለከቱ... አንደኛው ወጣት÷ኃይሉ ሽንቱን አቋርጦ ወደ መንገዱ በመዞር የሱሪውን ዚፕ ሳይዘጋ ታክሲዋን ለማስቆም በእጁ ያመለክታል ÷ ሁለተኛው ወጣት÷በላይ በቆመበት መሽናቱን እንደ ቀጠለ አንገቱን ወደ ታክሲዋ አዙሮ በአንድ እጁ ታክሲዋን ለማስቆም ምልክት ያሳያል... በአፉ የተለኮሰ ሲጋራ ይዟል/

1.1.2 / ከላይ እየበረረች ስትመጣ የነበረችው ታክሲ እዚያ አካባቢ ስትደርስ ፍጥነቷን እየቀነሰች ስትመጣ ትታያለች

# 1.2 /ከታክሲዋ ውስጥ/

1.2.1 / ከታክሲዋ ውስጥ ወንበሮቹ በሙሉ ተሳፋሪ ተቀምጦባቸዋል።

- ወያላው መስኮቱ ከተከፈተው ከኋለኛው ወንበር ጋ እንደ ቆመ ከሾፌሩ ጋር ሲነጋገር ሰዎቹ እያዳመጧቸው በመቃወም ያጉተመትማሉ

ሹፌር - / ታክሲዋን መንዳቱን እንደ ቀጠለ -ወደ ወያላው መለስ ብሎ ፖሊሶቹ ይኖሩ ይሆን እንዴ?

ወያላ- ባሁን ሰዓት! ኧረ በፍጹም

ሹፌር - /መሪውን ማጠምዘዝ እየጀመረ/ ጫናቸዋ ታ. ዲ. ያ

/ ተሳፋሪዎቹ በመቃወም ያጉተመትማሉ/

1.3 / ከታክሲዋ ውጪ - ከመንገዱ ላይ/

1.3.1 / ታክሲዋ እነ ኃይሉ ከቆሙበት አልፋቸው በሰላሳ ሜትር ርቀት አካባቢ ትቆማለች

ኃይሉ - /ከላይ ከቆመበት ቦታ - የሱሪውን ዚፕ እየዘጋና ጓደኛውን እንዲፈጥን እየነገረውና እያየው በሰከሩ እግሮቹ በሩጫ እርምጃ ወደ ታክሲዋ ይራመዳል።

በላይ - / ከቆመበት ቦታ መሽናቱን እንደ ቀጠለ - ታክሲዋ ወዳለችበት ዞሮ በአንድ እጁ መጣሁ መጣሁ በሚል ያመለክታል/

1.3.2 / ከታክሲዋ ውስጥ ያሉት ተሳፋሪዎች በመቃወም የጀመሩት ጉምጉምታ እየጠነከረ ጠብ አዘል የሆነ ንትርክ ሲነታረኩ ይሰማል/

## 1.4 / ከታክሲዋ ውስጥ/

አቶ ደምስ - / ከኋለኛው በር አጠገብ ካለው ወንበር ላይ ተቀምጠው ወደ ሹፌሩ እያዩ

ምነው አንተ ሰዎች መሆናችንን ተረሳህ እንዴ?

ሹፌር - / መለስ ብሎ/ እኔ ሰዎች አይደላችሁም መች አልኩና

ማህሌት - /ከኋለኛው ወንበር ላይ እንደ ተቀመጡ/

እንደ ሰርዲን ልታጭቀን አስበህ እየቆምክ?

ደምስ - ኧረ ቆይ ... ይሄን ያህል... ሕግ የሚባል የለም እንዴ...

ይሄ እኮ የሰውን ልክ አለማወቅ ነው

ሹፌር - /እንደ መቆጣት/ ምነው? ምነው አባባ...?

ደምስ - /አቋርጠውት በመመናጨቅ/ አባባህ? ተወኝ ስልህ!! ወገኛ ሁዋላ...

ሹፌር - እንዴ... በኋላ ጥለውት ለሚወርዱት ወንበር ምንድን ነው ይሄን ያህል!?

ደምስ - ብጥለውስ አ. ን. ተ. ?

ማህሌት -እኮ...ብንቀመጥበትም እኮ ስማ በከፈልንበት ገንዘብ መጠን ልንጓጓዝበት እንጂ ...

አንተ እንደ ፍላጎትህ እየጫንክብንና እያመናጨንከን ልታንገላታን በሚል

አልነበረም።

ሹፌር - ቢሆንም አባባ... መቼም ሁላችንም ኢትዮጵያዊ እስከ ሆንን ድ. ረ. ስ

ደምስ - /አቋርጠውት እየሳቁ/ አ. ቤ. ት አቤት ሂ. ቂ. ቂ ይህች የፈረደባት ኢትዮጵያ...

እሺ /ተሳፋሪዎቹ እየሳቁ... ያጉተመትማሉ

ሹፌር - ኧረ ምንድን ነው?! ... ጊዜው እየመሸ ስለሆነ እነኚህን ሰዎች ለመርዳት ብለን

ስናስብ እናንተስ ምን አለ ትንሽ ብታስቡ!

ማህሌት - /በሽሙጥ/ አንጎል እሚባል ስለሌለን ይሆናል ...?

/ተሳፋሪዎቹ ሁሉም ሳቁ/

# 1.4 / ከታክሲዋ ከውጪ እና ከውስጥ

1.4.1 / ከላይ ማህሌት የነ አቶ ደምስ ንግግር መስማቷን እንደ ቀጠለች -

በመሃል በመሃል ወያላው -የታክሲዋን በር ከፍቶ ከወረደ በኋላ እና በተራና በመስመር ሲጠብቅ ኃይሉና በላይ ተከታትለው በሰከረ የሩጫ እርምጃ እየተራመዱና ቁና ቁና እየተነፈሱ ሲመጡ ቆይተው ታክሲዋ ጋ ደረሱ ::

ወያላ - /በአንድ እጁ በላይን እንዲገባ እያመለከተ/ ና... ና/ ይልና... በሌላ እጁ ወደ አቶ ደምስ እያመለከተ አባባ ትንሽ... ትንሽ ጠጋ ይበሉ

ደምስ - / ከዘራቸውን ለጠብ እያመቻቹና ዞረው እየገላመጡት/ ዞር በል አንተ!? ልበቢስ ሁላ

በላይ - / ወደ ታክሲዋ መግባቱን እንደ ቀጠለ - ፊቱን ከአቶ ደምስ ወደ መሃለኛው ወንበር ላይ ከተቀመጠበት ሴቶች አጠገብ ሳያስፈቅድ ከተቀመጠ በኋላ .../ ወንበሩን ገዝተውታል እንዴ?

ኃይሉ - / ኃይሉን ተከትሎ ... የተለኮሰውን ሲጋራ በከንፈሩ ነክሶ እንደያዘ ... በሁለት እጆቹ የታክሲውን ግድግዳ ይዞ መግባት እንደ ጀመረ... /

ተሳፋሪዎቹ ከላይ በላይ ሲገባ - በመጠጥ የተበከለው ትንፋሹ ስላጠናቸው - በመቃወም እያጉተመተሙና አፍና አፍንጫቸውን እየሸፈኑና በሽሽት እየዞሩ ቆይተው አሁን ኃይሉ ሲጋራውን ይዞ ሊገባ መሆኑን ሲያዩ በንዴት እየተወራጩ ሲጋራውን እንዴት ነው!? ይጮሃሉ

በላይ - / ከተቀመጠበት ተንጠራርቶ - ከኃይሉ አፍ ላይ ሲጋራውን መንጭቆ ከወሰደበት በኋላ ወደ ውጭ ይጥለዋል::

# 1.5 /ከታክሲዋ ውጭ/

ወያላ - / የኃይሉን ወገብ እየገፋ ካስጠጋ በኋላ ተከትሎት ይገባና -በሩን ይዘጋል/

1.5.1 / ታክሲዋ ከኋላዋ በኩል እየታየች በሩ ከተዘጋ በኋላ - ዳገታማ የሆነውን ከአዲስ አበባ የሚያስወጣውን መንገድ ይዛ - ከእንጦጦ ጫካ ውስጥ ገብታ ትሰወራለች::

# ትዕይንት ሁለት

## 2. /ከሜዳው መሃል ባለው መንገድ ላይ/

2.1 / ታክሲዋ እየበረረች ስትመጣ - ከቅርበት እየራቀች መታየት እንደ ጀመረች…

2.1.1 /የትራፊክ ፊሽካ ይሰማል/

2.1.2 / ታክሲዋ ፍጥነቷን እየቀነሰች የመንገዱን ቀኝ እየያዘች

ጥጉን በመያዝ ሄዳ ተሰወረች

ትራፊክ - ታክሲዋ እንደ ተሰወረች … ከኋላ በኩል ሆኖ እየተከተላት ይታያል

2.2 / ከታክሲዋ ውስጥ

2.2.1 / ወያላ በሩን ከፍቶ ሲወጣ - ኃይሉ እና በላይ ከተቀመጡበት ተነስተው

ወያላውን ተከትለውት ይወርዳሉ/

/ተሳፋሪዎቹ በደስታ እፎይታ "እሰይ" ወለቁ እያሉ ያጉተመትማሉ/

ማህሌት - /በሞቀ ፈገግታ/ ማኖት እርስዎ ጌ. ታ. ው

አቶ ደምስ - አቤተ የኔ አንበሳ

ማህሌት - "አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል" የሚለውን ተረት ያስታውሱታል!?

አቶ ደምስ - /በመኩራራት/ እንዴታ "አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል" እንደሚባለው ወደ ትራፊኩና ወደ ሹፌሩ እየተጠቆመ … አታይልኝም እ. ን. ዴ / ትራፊኩ፥ ሹፌሩና እነ በላየ እየታዩ… (ትራፊኩ ደረሰኙ ላይ ከጻፈ በኋላ ደረሰኙን ቆርጦ ለሹፌሩ ሲሰጠው እየታዩ - አቶ ደምስ ከላይ የጀመሩትን ንግግር በመቀጠል ሲናገሩ ይሰማሉ…) አታይልኝም እንዴ…ስድስት ብር አገኘለሁ ብሎ ሲስገበገብ አንድ መቶ ስልሳ ስድስቱን ብር ሲያስተፋልኝ! ተሳፋሪዎቹ ሲስቁ ይሰማሉ።

/ ትራፊኩ የቆረጠውን ደረሰኝ ለሹፌሩ ሲሰጠውና ሹፌሩ ሲቀበል-

እጆቻቸው በቅርበት ይታያሉ/